# ዓረፈ

## ከዳኛቸው ወርቁ

ይስትማታል፣ ይስትማታል፣ ፍየሉ ሳሚቱን እንደተኛች፡፡ ግምባሯን አመማት መሰለኝ፣ ገና ብቅ ብቅ ያሉ በሚመስሉ ቀንዶቿ አንዴ በቀኝ አንዴ በግራ እያለች ትመክታለች፡፡ እረኛው በሁኔታቸው ይስቃል፣ ራቅ ራቅ ብለው መኪናው መንገድ ውስጥ ተኝተው የነበሩ ሌሎች ከበቶቹን እያስነሳ አንድ አህያ ይንደባለሳል፣ አመንገድ መካከል እምቢያውን ሳዘቅዛቂዋ ፀሐይ እያሳዩ ጭሬዎች አጠገቡ እነበረው ባሕር ዛፍ ቅርንጫፍ ሳይ ተቀምጠው ጀርባው መካከል የሚንተገተገውን ገጣባ ይጠባበቃሉ፡፡ ሆዷ ቅብንን ያለ የረኛው ውሻ በምናለብኝ አስተናኘት አፏን አስፋልቱ ሳይ ተክሳ ፀሐይዋን ትመለካከታለች፡፡ እያፈገፈገ ይስትማታል ፍየሉ ሳሚቱን እያፈገፈገ ይስትማታል፡፡ ከተነሣች እንኳ በኋላ፣

ቀስ በቀስ ሁሉም -- -- አህያውም ውሻውም ጭምር ከየነበሩበት ተነስተው ሲያበቁ መንዳት ጀመረ እረኛው ሳማቱ ወደፊት አመራች፡፡ እያፈገፈገ ይወጋት የነበረውም ፍየል እንደመንደርደር እንደመንደርደር እያለ ተመሳልሶ ከኋላዋና ከጎኗ አንዴ ሁለቴ ስተም ስተም አረጋትና ፈግፈግ ፈግፈግ እያለ ከነጭራሹ ከሁሉም ኋላ ቀርቶ ራሱን ቁጭ ብድግ ውዝውዝ እያደረገ ከሩቅ ተከተላት፡፡ -- -- ልጥልጥ በርኖስ የሚመስለው የሳምዋ ጀርባና ነጣ ያለ አረሞጫ መሰል የፍየሉ በጠራራው ፀሐይ ሥር እየወጡ እየጠለቁ እየተነቦገቦጉ ራስ መኮንን ምንጭ አገጠብ ያለውን ዳገት ተያያዙት፡፡ እኔም ወዳርባ ደረጃዬ አመራሁ፡፡

ለወትሮው /ዛሬስ መቼም እግረ መንገዴን ነው፣ የምስክር ወረቀቴን ሳጎቴ አሳይቼ መመለሴ ስለነበረ/ ሁለተኛ ደረጃዬን ጨረስኩ ለማለት ያስቻለኝ ት/ቤት ስለነበረ /ምንም እንኳ የተማርኩበት የመጨረሻውን ዓመት አስራ ሁለተኛውን ክፍል ብቻ ቢሆንም/ ምናልባትም ናዝሬት ት/ቤት አጠገብ ስለሆነም እንደሆን እንጃ ብቻ ለወትሮው ካለፍ አገደም ወደ አሜሪካን ኢንስቲቲዩት ማሻቀብ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ እና ዛሬም ወዳርባ ደረጃ ሳመራ እንግዲህ የተለየ ነገር የተለየ ምክንያት አልነበረኝም፣ የልማዴን ማድረሴ ነበር፡፡

ስለዚህ ቀስ እያልኩ ቀርቤ አርባ ደረጃዬን ተያያዝኩት፣ እንደልማደ እንዳጋጣሚ ሆኖ ከልማደ ወጪ ከሥሩ ጀምሮ እየቆጠርኩ አእምሮዬ ሥራ ፈትነትን መጥላቱ ካልሆነ በቀር ምን እንዳስመለከተኝ ሳላውቅ ቆጠራውን፣ እናትም ደረሰሁ፡፡

እዚህ ሳይ ነው እንግዲህ ሰው ያልደረሰበት አዲስ ነገር የገለጠልኝ የመሰለኝ ወደ ግራ አግድም ተመልሼ ሰባ ደረጃን እንድቆጥር የተገደድሁ፣ እየቆጠርሁ የወረድሁት እንደገናም ተመልሼ እየቆጠርኩ የወጣሁት፡፡ እዚህ ሳይ ነው አርባ ደረጃውው ሰባ አለ መሆኑን ማወቄ አዲስ ነገር የመሰለኝ፡፡ እዚህ ሳይ ነው በየደረጃው ዳር ዳር ሽቅብና ቁልቁል ያለውን ችፍግ ያ የሰንሰለ አጥር አልፎ አልፎ አንዳንድ ነገሩን ያየሁበት፤ የተቻኮሉ በመምሰል ቀሚሳቸውን በተን አርገው የተመቀመጡ አዛውንቱን ያንድ ጉልበት ቁምጣውን ወደ ሙሳው በኩል ሰብሰብ አርጎ ይዞ እጉድባው ውስጥ ያደረጠ ጉብለን፣ አልፎ አልፎም ማርያምና ገብሬልን፣ ጊዮርጊስንና ሚካኤልን ከአፉ ባለመለየት የሚያይ መሰል ዓይኖቹን በራሱና ባንገቱ ሳይ የተቆለለ ጭርንቁሱን አሳልፎ እያዥረገረገ መብት ያሰጠውን የማይዝል፣ የማይደክም ጠምራራ ጣት የለሽ እጁን ወይም እግሩን የሰው ኮቴ በሰማ ቁጥር የሚያወዛውዝ ፍጥረቱን ደግሞስ ያንን እፊቱ ስደርስ አፉን ተጣድፎ ለማስለቀቅ ወደ አጠገቤ ፊቱ ብሎ ወዲያው መስመን ጀምሮ ሳልሰጠው ባልፍ ወዲያው መሳደብ የጀመረውን ያየሁት መሳደብ የጀመረውን ያየሁት አስታውሳለሁ እጄ እኪሴ ገባና የምስክር ወረቀቴን መዥርጦ ወጣ፡፡ «የአሜሪካን ኢንስቲቲዩት.... » «...በሚያጠግብ ውጤት አስራ ሁለተኛ ክፍል የሚሰጠውን ትምህርት ጨርሶአል.... »

ሲለኝ፡፡ አደረጃዎቹ ሁሉ አናት ከሚገኙት ሁለተ አራት መአዘን ድንጊያዎች አጠገብ ስደርስ ወጥሮኝ አገኘሁት እኔም፣ እንደሌሎቹ ሰዎች አንዱን ከሌሳ አድርጌ አዎ ቁልቁል ተንደረደረ፡፡

አባቴን ፊታውራሪ አበበ ጉግሣን በጣም ደስ በሏቸው ነበር፡፡ የምስክር ወረቀቴን ይዤ እቤቴ የገባሁለት፡፡ እንግዲህ አስቡት ዓመቱ ከተጋመሰ በኋላ ነው በስንት ጭቅጭቅ ፈቅደውልኝ ገብቼ አስራ ሁለተኛን ክፍል ለመጨረስ የቻልኩት፡፡ በጣም ደስ ብሏቸው ነበር፡፡ «ግዴለም እንግዲህ አረፍ ብለህ ትገባለህ ዩኒቨርሲቲው፣ መጣደፍ አያሻም» ብለው ነበር፡፡ ድካሜ እንኳ ሳይቀር አውቀውልኝ፡፡ ዩኒቨርሲቲ በሰጠው ፈተና ካምስቱ የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ብቻ ማለፌን አልነገርኳቸውም ነበር፡፡ አዎ ደስታቸውን ወደ ኀዘን እንዳለውጥባቸው ደግሞሳ አምሳ ብር ተፈቅዶልኝ ነበር፡፡ በወር ዩኒቨርሲቲ እስክገባ ድረስ፡፡ ስምን ይቅርብኝ እንኳንስ /ምናልባት መውደቄን ስነግራቸው ተናደው ሳይከለክሉኝ ስለማይቀሩ/ እንኳንስ ከልክለውኝ ሰጥተውኝም አልሆነልኝም በኔ ዘዋሪነት፡፡ እርግጥ እናቴ አልፎ አልፎ ትንሽ ገንዘብ ትሰጠኝ ነበር፡፡ በሰጠችኝ ቁጥር «ሁለተኛ አገኛለሁ ብለህ አፍክን እንዳታበላሽ፣ ዕወቅበት» እያለች ደረሶ ፊቴ በረዘመ ቁጥር ማወቋና አንጀቷ መራራቷ ሳይቀር፣

ታዲያ እንግዲህ መቼም እንዲያም ሆኖ ተስፋ አልቆረጥሁም ነበር ዩኒቨርሲቲ ስለመግባቴ፡፡ ዛሬ ይኸው ተበራትቼ ወደ ቅጥር ግቢው ሄድሁ፡፡ ለግላጋ መሳይ ሰው የምዝገባው ኃላፊ ናቸው ተብለው አነጋገሩኝ፡፡ ገና ቁመናዬን ሲያዩ በሁኔታቸው እንዳየሁት ብገባ ፈቃዳቸው መሰለኝ፡፡ «ምን ሳርግ እንዴት ብዬ ልርዳህ» አሉኝ ደጋግመው፡፡ ድምፃቸው ያባቴን መስለኝና ካንጀታቸው መሆኑ ገባኝ፡፡ .... «እንዴት ብዬ ልርዳህ... » አይ ጥሩ ሰው ናቸው፡፡ -- -- ሴትየዋስ ምክትሏ-- --«ድንቡሼ ገላ» የምንላቸው ዓይነት ናቸው፡፡ «ኬክ» ምልላቸው አችላለሁ እንግሊዝ ጽ/ቤት ተምሪያት በነበረ አማርኛ ስገባ ብቻ ትኩር ብለው ባዩኝ ጊዜ እንደነጸብራቅ ተወርውሬ ባይናቸው የገባሁ መሰለኝና «ግድለም ዋናው መዝጋቢ ነግረውኛል እርስዎን ደሞ ማስቸገር ይሆንብኛል ግደለም» አልኩኝና ተርበትብቼ ወጣሁ፡፡ ...«የኔ የልጅ እኮ አቋቋሙ ብቻ ያበቃል» ሲሉ እሰማቸው ነበር አባቴ፡፡ -- --ስወጣ ብድግ ብለው እንደመጨበጥ እጃቸውን ዘርጋ ያረጉ መሰለኝ ምክትሏ፡፡

አቆለቆለኩ ወደ ፓርላማ ገደማ፡፡ ማርያምን ተሳለምኩ፣ አለመትሮዩ... በተራዛሚ መንገድ-- -- መንበረ ባትርያርኩ ድረስ ግቢዋን እየተመለከትኩ-- --«ኧረ አባክሽ አለሁ በይኝ አልኳት»፣ እንዳጋጣሚ እናቴ ካለፍ አገደም ትለው የበረው ትዝ ብሎኝ፡፡ ዝቅ አልኩኝ ደሞ፣ የድል ሐወልት እናቱ ገደማ የማገኘው ሰዓት ስምንት ሰዓት ከሃያ አምስት ላዩ መቆሙ ያለወትሮው አእምሮዬ ውስጥ ተሳገና አልወጣም አለኝ፣ እወስጥም እንደልማድ የቆመ መስለኝና እንደሰድቻ መታኝ፡፡

በፍጥነት በመራመድ ሥላሴ ሕንፃ ዘንድ ደረስሁ፣ ከራሴ የምሮጥ ይመስ፡፡ አንድ ፊያት መኪና በኃይል ሲመጣና በሥላሴ ካቴድራል ትይዩ ለእግር መንገደኞች ከተፈቀደው መስመር ውስጥ አንድ ድሪቶ አንስቶ ካጎነው በኋላ እዚያው አጠገብ መልሶ ሲዘረጋው አያሁኝ፡፡ ራመድ ራመድ ብዬ ቀረብኩት፣ ድሪቶ ኖሮአል እውነትም እንደራስ ቆብ የቶረረው-- --

የሥላሴን ሕንፃ ጨርሶ የቆርቆሮ አጥር እሚጀምርበት አጠገብ ሰዎች መሰብሰብ ጀመሩ፡፡

«ሞቷል ሞቷል»

«ተሸክሞ እኮ ነው እስከዚህ ያወጣው»

«ልክ አሁን በኃይል ሲያቆም ነው ተኝሸራቶ ሲወርደ የቻለው»

«እንዴት ሳይዋል እስከዚህ ድረስ ተሸከም አመጣው?»

«ፈረንጁ እኮ በመኪናዬ ሆስፒታል አሳደርስም አለ»

«ወደ አሜሪካን ቆንሲሉ ስልክ ደውሏል ይላሉ» እያሉ እያስፋኝ አሸቆለቆሉ፡፡ እኔ ግን እዚያው እድሪቶው አጠገብ ብዙ የቆየሁ መሰለኝ፡፡ የፓርላማው ሰዓት አስራ ሁለት ጊዜ እንቃጨለ ስድስት ሰዓት ማለቱ ኖሮአል እናቴን የሚመስሉ አዛውንት ለብቻቸው እየተነጋገሩ በአጠገቤ መጡ፣ እየተነጋገሩ በአጠገቤ መጡ፣
«እሱስ ዓረፈው-- -- ዓረፈው-- --

«ዓረፈው-- --» ያያሉ ትክ ብዬ አየኋቸው -- -- ትክ ብለው አዩኝ፣ በመጡበት ዓየነት ፊታቸውን ገደል እንዳስመሰሉ .... «ዓረፈ» ብለው አንገታቸውን በመነቅነቅና በማቀርቀር መንገዳቸውን ቀጠሉ፤